# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅ የመረጃ ምንጭ: ACA, ACA-RA, ACI, ACH, ACH-RA, GKA-RA
ኃላፊነት ያለው ቢሮ: Office of District Operations; Office of Human Resources and Development

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች Title IX ጾታዊ ትንኮሳ ምርመራ

I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ Title IX ጾታዊ ትንኮሳ ምክንያት ለሚነሱ ቅሬታዎች አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት ሂደቶችን ለመደንገግ።

II. ዳራ

ጾታዊ ትንኮሳ 1972 እና 1991 የተሻሻለውን የ1964 የሲቪል መብቶች ህግ "Title VII" መጣስ ስለሆነ በሥራ ላይ መድልዎ እንደተደረገ ተቆጥሮ እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል። ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ የሥራ ቅጥር አድልዎ ውንጀላዎች Regulation ACA-RA መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ፣ እና የባህል ብቃት ድንጋጌ መሠረት ሪፖርት መደረግ አለበት።

Title IX በተለምዶ በተማሪዎች ላይ ተፈጻሚነት እንዳለው ቢታወቅም፣ በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለጹት አንዳንድ ሁኔታዎች፣ በሰራተኞች ላይ የሚደርስ ወሲባዊ ትንኮሳ በዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት እንደተተረጎመው Title IX ስር ሊተገበር ይችላል። በ 2020 የዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት Title IX የፆታዊ ትንኮሳ ቅሬታዎች ምላሽ እና የምርመራ ፕሮቶኮል Title VII ስለ መድልዎ ክሶች ምላሽ እና የምርመራ ፕሮቶኮል የተለየ መሆኑን ገልጿል። Title IX ፕሮቶኮሎች በዚህ ደንብ ውስጥ ተገልፀዋል።

አንዳንድ የፆታዊ ትንኮሳ ዓይነቶች የወንጀል ድርጊትን ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህም የወንጀል ቅጣት ያስከትላል።

ሰራተኞች፣ ተቆጣጣሪዎችን ጨምሮ፣ መመሪያን፣ ድጋፍን እና/ወይም ከወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ተገቢ ያልሆነ የወሲብ ባህሪ ጋር የተያያዘ መረጃ ከሰራተኛ እርዳታ ፕሮግራም (EAP) እንዲፈልጉ ይመከራሉ። የሰው ሀብት ልማት ቢሮ (OHRD)፣ የሥነ ሥርዓት ማስከበር እና ምርመራ ክፍል (DCI)፣ ወይም በዲስትሪክት ኦፐሬሽን፣ የተማሪ ደህንነት እና ሥነ ሥርዓት ማስከበር ቢሮ Title IX አስተባባሪ።

III. ትርጉም

A. ፆታዊ ትንኮሳ1964 የዜጎች መብቶች ህግ Title VII እና/ወይም 1972 እና 1991 የ1972 የትምህርት ማሻሻያ ህግ Title IX መጣስ ሲሆን ይኼውም:

1. ጾታዊ ትንኮሳ Title VII በተገለፀው መሠረት አንድ ግለሰብ ያልተፈለገ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከተፈፀመበ(ባ)ት፣ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ውለታ መጠየቅ፣ እና ሌሎች ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው ተገቢ ያልሆነ የቃል፣ የጽሁፍ ወይም አካላዊ ባህሪ መጠየቅ እንደ ስራ መድልዎ እርምጃ ያስወስዳል። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የወሲብ ትንኮሳ የሚሆነው—

a) የአንድ ግለሰብ የስራ ጊዜ በግልፅም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ አይነት ባህሪ ለመገዛት ቅድመ ሁኔታ ተፈፅሟል፣ ወይም

b) በግለሰብ ለእንዲህ አይነት ባህሪ መገዛት ወይም አለመቀበል እንደዚህ አይነት ግለሰብን ለሚመለከቱ የስራ ቅጥር ውሳኔዎች መሰረት ሆኖ ያገለግላል፣ እና/ወይም

c) እንዲህ አይነት ባህሪ የግለሰብን ስራ አፈጻጸም ያለምክንያት ጣልቃ የመግባት ወይም የሚያስፈራ፣ ጥላቻ ወይም አፀያፊ የስራ አካባቢ የመፍጠር አላማ ወይም ውጤት አለው።

2. Title IX ድንጋጌ መሠረት ፆታዊ ትንኮሳ እንደ ፆታ መድልዎ ተደርጎ በዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት እንደተተረጎመው አንድ ግለሰብ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ካጋጠመው/ካጋጠማት እርምጃ የሚያስወስድ ይሆናል፦

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCP) ሰራተኛ ባልተፈለገ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፣ እርዳታ፣ ጥቅማጥቅም ወይም አገልግሎት ግለሰብን መጠየቅ።

b) በደህና ሰው የሚፈፀም ያልተፈለገ ምግባር በጣም ከባድ፣ ከግብረገባዊነት ያፈነገጠ፣ እና በተጨባጭ አስጸያፊ በመሆኑ አንድን ግለሰብ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ በእኩልነት እንዳይጠቀም/እንዳትጠቀም የሚከለክል፣ Title IX ደንብ ላይ እንደ አካባቢው፣ የክስተቱ ሁኔታ፣ ወይም ሁኔታዎች በዚህ ላይ MCPS በሁለቱም ቅሬታ አቅራቢ እና ተጠያቂው(ዋ) ጾታዊ ትንኮሳ በተከሰተበት ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ያደርጋል።

c) በዩናይትድ ስቴትስ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ህግ ላይ በተገለፀው መሰረት "ፆታዊ ጥቃት"፣ "በጓደኝነት አብሮ መውጣት ላይ የሚፈፀም ጥቃት"፣ "የቤት ውስጥ ጥቃት" ወይም "እያሸመቁ/እያደቡ መከታተል"።

3. ሶስተኛ ወገን ማለት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ወይም ተማሪ ያልሆነ(ች) MCPS የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ወይም MCPS ንብረት ላይ የሚገኝ/የምትገኝ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስልጣን ወይም ቁጥጥር ያለ(ች) እና ያልተገደበ(ች) ማንኛውም ሰው ነው፥ ይኼውም፦ MCPS ንብረት ላይ መስተጋብር ያላቸው ሻጮች፣ ተቋራጮች፣ አሰልጣኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አማካሪዎች እና ሌሎች ሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች ናቸው።

## III. ቅደም-ተከተል

### A. የሰራተኞች ማመልከቻ

1. የቦርድ ፖሊሲ ACI፣ ስለ MCPS ሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ; MCPS ደንብ ACA-RA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊ እኩልነት እና የባህል ብቃት; ይህ ደንብ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ጋር በተያያዙ የፆታዊ ትንኮሳ ክስተት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወይም ከተመሳሳይ ጾታ ጋር በሁለቱም ፆታ በሚደርስ ጾታዊ ጥቃት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ መፈፀም ከህግ፣ ከቦርድ ፖሊሲ እና MCPS ደንቦች ጋር የሚጋጭ ነው።

2. የፆታዊ ወከባ ድርጊቶችን ማወቅና ወድያውኑ ተፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ የተቆጣጣሪ

ሰራተኞች ሃላፊነት ነው።

B. የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታ

1. ጾታዊ ትንኮሳ እንደደረሰባቸው የሚያምኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ጉዳዩን በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ሶስተኛ ወገንም ስለ ጾታዊ ትንኮሳ ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል።

2. ሪፖርቱ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል።

3. MCPS የሰራተኞች እና የሶስተኛ ወገን የፆታዊ ትንኮሳ ጥያቄዎችን ጨምሮ የሚደረጉ ምርመራዎችን ምስጢራዊነት ይጠብቃል፣ከሚመለከታቸው ህጎች እና MCPS እንደዚህ ያሉ ቅሬታዎችን የመመርመር እና የመፍታት ሀላፊነት ጋር በተጣጣመ መልኩ ይጠብቃል።

4. አንድ ግለሰብ አንድን ክስተት በመጠቆም ወይም በተከሰሰው ክስተት ላይ ምርመራ ሲካሄድ በመተባበር ምክንያት ምንም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ አይኖርበ(ባ)ትም።

C. Title VII የወሲባዊ ትንኮሳ ቅሬታ ምርመራ

1. በሰራተኛ ወይም በሶስተኛ ወገን Title VII ስር የሚቀርብ የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታ ቅፅ 230-39፣ በመሙላት የአድልዎ ቅሬታ ወይም የስራ ቦታ ማስፈራራትና ጉልበተኝነትን ሪፖርት ሊደረግ ይችላል። DCI@mcpsmd.org ኢሜል በመላክ፣ በቀጥታ DCI ማነጋገር፣ ወይም EAP ወይም ከርእሰመምህራቸው/ተቆጣጣሪያቸው ጋር በመመካከር፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ጉዳዩን ወደ DCI ይመሩታል።

2. Title VII የጾታዊ ትንኮሳ ቅሬታ ምርመራ MCPS ደንብ ACA-RA፣ መሠረት አድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት ሂደትን ይከተላል።

D. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታ ምርመራ

1. Title IX የፆታዊ ትንኮሳ ቅሬታ እንዲመረመር ለመጠየቅ ሰራተኛው(ዋ) MCPS ቅጽ 0109.22 EGPS፣ Title IX የአድሎዊነት መደበኛ ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ መሙላት እና ወደTitle IX አስተባባሪ ማቅረብ አለበ(ባ)ት። TitleIX@mcpsmd.org፣ እርሱ(ሷ) ለ DCI ያቀርባል/ታቀርባለች።

2. Title IX መደበኛ የጾታዊ ትንኮሳ ቅሬታ የሚከተሉት ግዴታዎች ወይም ልል የሆነ ውድቅ የመሆን ተፈጻሚነት አለው።

   a) መደበኛ ቅሬታን በሚመለከት ተፈጻሚነት የሌላቸው ግዴታዎች

      (1) Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረግ ያለበት/ባት–ሁኔታ

         (a) መደበኛ ቅሬታ የተከሰተው ድርጊት Title IX ጾታዊ ትንኮሳን ትርጉም የማያሟላ ከሆነ፣ ባህሪው የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ወይም

         (b) ድርጊቱ የተፈጠረው MCPS የትምህርት ፕሮግራሞች/ተግባራት በሚከናወኑበት ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ።

(2) መደበኛ ቅሬታን ውድቅ ማድረግ ACA-RA ደንብ፣ መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት፣ እርምጃ መውሰድን አይከለክልም። MCPS የተማሪ የስነምግባር ደንብ; ወይም MCPS የሰራተኛ የስነምግባር ደንብ።

b) መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረጊያ በግል የሚወሰን ሁኔታ

(1) Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረግ የሚ(ምት)ችለው–

(a) አቤቱታ አቅራቢው(ዋ) ወደ Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታውን ማንሳት መፈለጉን/ጓን በፅሁፍ ከገለፀ/ች፤ ወይም

(b) መልስ ሰጪው/ዋ አሁን ላይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገበ/ች ወይም የተቀጠረ/ች ካልሆነ፤ ወይም

(c) MCPS የቀረበው መደበኛ አቤቱታ ወይም ተፈፅሟል የተባሉት ክሶች ላይ ከውሳኔ ለመድረስ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ከመሰብሰብ የሚያግዱ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉ ነው።

3. መደበኛ ቅሬታ ሲደርሰው ከገመገመ በኋላ፣Title IX አስተባባሪ/ተወካዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች የጽሁፍ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል/ትሰጣቸዋለች እና መርማሪ ይመድባል።

4. ተጠያቂነትን በተመለከተ ውሳኔ ላይ ለመድረስ መርማሪው(ዋ) ማስረጃ ይሰበስባል/ትሰበስባለች። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች መግለጫዎችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች አስረጂ እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ጨምሮ ለመርማሪው(ዋ) ማስረጃ ለማቅረብ እኩል እድል ይኖራቸዋል።

5. በምርመራው ማጠቃለያ ላይ ተጠያቂነትን በሚመለከት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተጠርጣሪ ለተከሰሰ(ች)በት ድርጊት ጥፋተኛ ነው/ነች ተብሎ አይገመትም።

6. የምርመራ ሪፖርቱ ከመጠናቀቁ በፊት፣ ከክሱ ጋር በቀጥታ የተያያዙ ማስረጃዎችን መርማሪው ለእያንዳንዱ ወገን እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አማካሪ የሚላክ ማስረጃ ጋር እየተገናዘበ ግምገማ የሚደረግበት ጊዜ መኖር አለበት። እያንዳንዱ አካል የፅሁፍ ምላሽ እንዲያቀርቡ 10 ቀናት ይሰጣቸዋል።

7. ከማስረጃ ግምገማው በኋላ፣ መርማሪው(ዋ) የተፃፉ ምላሾችን በመገምገም የምርመራ ሪፖርት ያዘጋጃል።

8. የምርመራ ሪፖርቱ ሲጠናቀቅ፣ እያንዳንዱ አካል እና የሚመለከተው አማካሪ ሪፖርቱን ለመገምገም እና የጽሁፍ ምላሽ ለመስጠት 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ይኖራቸዋል።

9. ከምርመራ ሪፖርቱ ግምገማ በኋላ፣ DCI ዳይሬክተር የምርመራ ሪፖርቱን እና ማንኛውንም የጽሁፍ ምላሾች ይገመግማል እና ለ OHRD ሃላፊ አስተያየት ይሰጣል፣ እሱም እነዚህን ሰነዶች መርምሮ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የተጠያቂነት ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔው በአንድ ተመሣሣይ ጊዜ ለሚመለከታቸው ወገኖች ይላካል።

10. በተጠርጣሪነት የቀረበው ክስ ድርጊት Title IX ላይ የሚወድቅ ጾታዊ ትንኮሳ መሆኑ የሚያመዝን ከሆነ ውሳኔ የሚካሄደው በማስረጃ ቅድመ ዝግጅት ነው።

E. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት

1. በ OHRD ኃላፊ የተሰጠን የተጠያቂነት ውሳኔ በሁለቱም ወገኖች ለዋና ኦፕሬሽን ኦፊሰር (COO)/ተወካዩ ይግባኝ ማለት ይችላል።

2. ውሳኔው በተሰጠ 10 ቀናት ውስጥ በሚመለከተው ወገን ይግባኝ መቅረብ አለበት።

3. ሀላፊነት/ተጠያቂነት መውሰድ ውሳኔ ላይ፣ ወይም የመደበኛ አቤቱታ ውድቅ ማድረግ ላይ ከሁለት በአንዱ ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ ነው፡-

    a) የምርመራውን ውጤት የሚያዛባ የአሰራር ግድፈት።

    b) የጉዳዩን ውጤት ወይም ተጠያቂነትን ወይም ከተጠያቂነት የማሰናበት ጊዜን በተመለከተ በውሳኔው ወቅት ያልቀረቡ አዳዲስ ማስረጃዎች።

    c) Title IX አስተባባሪ፣ መርማሪ ወይም ውሳኔ ሰጪ(ዎች) የጉዳዩን ውጤት የሚያዛባ የጥቅም ግጭት ወይም አድልዎ ከነበረው።

4. የሰለጠነ COO አጣሪ ባለሙያ ይመደብለታል።

5. ይግባኝ ከቀረበ፣ COO አጣሪ ባለሙያ በይግባኝ ተጠሪ ለሆነ ወገን በጽሁፍ ያሳውቃል።

6. ሁለቱም ወገኖች ውሳኔውን በሚመለከት በፅሁፍ ቃላቸውን እንዲሰጡ እድል ይሰጣቸዋል።

7. የጽሁፍ ቅሬታ በደረሰው 10 ቀናት ውስጥ፣ COO አጣሪ ባለሙያ ---

    a) የምርመራ ሰነዶችን እና በሁለቱም ወገን በጽሑፍ የቀረቡ ማንኛውንም የክርክር ጭብጦችን ይገመግማል/ትገመግማለች፤

    b) የይግባኙን ውጤት እና ምክንያቶቹን የሚገልጽ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት፣ለሚመለከታቸው ወገኖች ወዲያውኑ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲደርሳቸው ማድረግ፣ እና

    c) በቦርዱ ፖሊሲ BLB፣ ይግባኝ እና የችሎት አሰራር ደንቦች እና የስቴት ህግ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ወደ ቦርድ ይግባኝ ለማለት ለሚመለከታቸው ወገኖች ውሳኔውን እና መብታቸውን ያሳውቃል።

F. Title IX የፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታ ኢ-መደበኛ ውሳኔ

1. ሀላፊነት/ተጠያቂነት የመውሰድ ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ፣ ማንኛውም ወገን/አካል ለመደበኛ አቤቱታ ኢ-መደበኛ ውሳኔ እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል።

2. በኢ-መደበኛ ውሳኔ ላይ ተሳትፎ ማድረግ በግል ፈቃደኝነት ላይ ይወሰናል። ሁለቱም ኢ-መደበኛ የመፍታት ሂደት ላይ በፈቃደኝነት የጽሁፍ ስምምነት መስጠት አለባቸው።

3. በሰራተኛ ተፈፀመ ለተባለ የተማሪ ፆታዊ ትንኮሳ ክሶች የቀረበ መደበኛ አቤቱታን ለመፍታት የኢ-መደበኛ ውሳኔ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

**ተዛማጅ ምንጭ፡-** Civil Rights Act of 1964, Title VII; Title IX of the Education Amendments Act of 1972, as amended (34 C.F.R. §§ 106.44, 106.45); Equal Employment Opportunity Commission (EEOC) Sexual Harassment Guidelines (29 C.F.R. § 1604.11); Violence Against Women Act of 1994, 34 U.S.C. § 12291; Annotated Code of Maryland, Education Article § 7-424; Memorandum of Understanding; MCPS Student Code of Conduct; MCPS Employee Code of Conduct

**የደንቡ ታሪክ፡-** አዲስ ደንብ፣ ፌብሩዋሪ 1, 2023።

[1] ሙሉ ርዕስ፡ ትምህርት ቤት ላይ ለሚፈጠሩ ክስተቶች የህግ አስከባሪዎችን የሚያካትቱ ክስተቶችን የሚመለከቱ ፕሮቶኮሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ እና ሌሎች ኤጀንሲዎች የማህበረሰብ ተሳትፎ ኃላፊን የሚመለከት ፕሮግራም እና ሌሎች የህግ አስከባሪ ምላሾች የመግባቢያ ሠነድ ላይ ተቀምጠዋል፣ ኤፕሪል 4, 2022። (የመግባቢያ ሠነድ)

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦  U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org